# - 37 -

## ባህሩ ይከፈትልን ዘንድ[2]

ነቢዩ ሙሳ (ዐ.ሰ.) በመለኮታዊ ተዓምር ታግዘው አምባገነኑን ፊርዐውን በአደባባይ በግልጽ ማስረጃ በረቱት ጊዜ ፊርዐውን ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ (ሱ.ወ.) እጅ ለመስጠት አሻፈረኝ አለ። እናም ኃይሉንና ጉልበቱን ተማምኖ በሥልጣን ሊገዳደረኝ ነው ብሎ ያሰበውን ነቢዩ ሙሳን (ዐ.ሰ.) ማሳደድ ያዘ። ሽሽቱ ከግብፅ ምድር ወደ ቀይ ባህር አቅጣጫ ነበር። ሙሳ (ዐ.ሰ.) ሸሹ። ፊርዐውንም ሠራዊቱን ይዞ ደካማውን ሙሳ ተከተላቸው። ለሽሽት የተዳረጉት ሙሳ በመጨረሻም ከባህር ጋር ፊት ለፊት ተገናኙ። ባዶ እጃቸውን ታላቁን ባህር ተጋፈጡ። ከኋላቸው ደግሞ የፊርዐውን ኃያል ሠራዊት እየደረሰባቸው ነው። የሙሳ ተከታዮች ተጨነቁ። ከፊሎቹ አጉረመረሙ። ሽንፈታቸው የተቃረበ መሠላቸው። ዙርያቸውን ሽንፈት ብቻ ታያቸው። ሁኔታውን አላህ (ሱ.ወ.) በቁርአኑ ገልፆታል፡-

﴿ فَلَمَّا تَرَٰٓءَا ٱلۡجَمۡعَانِ قَالَ أَصۡحَٰبُ مُوسَىٰٓ إِنَّا لَمُدۡرَكُونَ ﴾

**«ሁለቱም ጭፍሮችም በተያዩ ጊዜ፣ የሙሳ ጓዶች "እኛ (የፈርዖን ሰዎች) የሚደርሱብን ነን፣ አሉ።»** (አሽ- ሹዐራእ : 61)

ግና ነቢ ሙሳ (ዐ.ሰ.) የተለየ ሀሳብ፣ የተለየ እይታ ነበራቸው። የሚመሩት በመንፈሳዊ ምልከታ ነውና እገዛ አላቸው። በርግጥም ሽንፈት እውነት ከሚመስል ዓለማዊ ብዥታ ባሻገር ተመለከቱና ድልና መሻገርን ተመለከቱ። ልባቸው ከፍ ካለው አምላክ ጋር ተሳስራለችና። የማይቻል ከሚመስል ሁኔታ ጀርባ ድልና ነፃነት ቦግ ብሎ ታያቸው።ሙሳ አምላካቸውን ብቻ ነበር የተመለከቱት። እናም እንዲህ አሉ፡-

﴿ قَالَ كَلَّآۖ إِنَّ مَعِيَ رَبِّي سَيَهۡدِينِ ﴾

**«ተው! ጌታዬ ከእኔ ጋር ነው፣ በእርግጥ ይመራኛል።»** (አሽ ሹዐራእ : 62)

አላህም በርግጥ መራቸው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፡-

﴿ فَأَوۡحَيۡنَآ إِلَىٰ مُوسَىٰٓ أَنِ ٱضۡرِب بِّعَصَاكَ ٱلۡبَحۡرَۖ فَٱنفَلَقَ فَكَانَ كُلُّ فِرۡقٖ كَٱلطَّوۡدِ ٱلۡعَظِيمِ ﴿٦٣﴾ وَأَزۡلَفۡنَا
ثَمَّ ٱلۡأٓخَرِينَ ﴿٦٤﴾ وَأَنجَيۡنَا مُوسَىٰ وَمَن مَّعَهُۥٓ أَجۡمَعِينَ ﴿٦٥﴾ ثُمَّ أَغۡرَقۡنَا ٱلۡأٓخَرِينَ ﴾

2 ፀሐፊዋ ከሑስኒ ሙባረክ ውድቀት በኋላ የመጣዉን ነፃነት አስመልክታ የፃፈችው ነው። የተወሰነ ሀሳቡ ለአገራችን አንባቢያን እንዲመች ተብሎ ተቆርጧል።



CamScanner
CamScanner

**«ወደ ሙሳም፥ ባሕሩን በበትርህ ምታው፤ ስንል ላክንበት። (መታውና) ተከፈለም፤ ክፍሉም ሁሉ እንደ ታላቅ ጋራ ኾነ። እዚያም ዘንድ ሌሎችን አቀረብን። ሙሳንና ከርሱ ጋር ያሉትንም ሰዎች፤ ሁሉንም አዳን። ከዚያም ሌሎቹን አሰጠምን።» (አሽ-ሹዐራእ : 63-66)**

ዛሬ ላይ የሙስሊሙ ኡማ ሁኔታ ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ ነው። ከባህሩ ጋር ተጋፍጠናል። ፊት ለፊት ተፋጠናል። አምባገነኖች ከኋላ ያሳድዱናል። ዛሬ ላይ ሽንፈት ብቻ የሚታያቸው አሉ። ግና ከመከራው ባሻገር መውጫ መንገድ እና ተስፋም የሚታያቸው አሉ። እንዲሁ ዛሬም እንደ ነቢዩ ሙሳ ሁሉ "ጌታዬ ከእኔ ጋር ነው፤ እሱም ይመራኛል።" የሚሉ አሉ።

አንዳንድ ሰው ሊገርመው ይችላል። ከግርምትም አልፎ ሊጠይቅ ይችላል። ለምንድነው በዚህ ዓይነት መልክ ታሪክ ራሱን የሚደግመው። ከሺህ ዓመታት በፊት የነበረ ክስተት ከዛሬው ሁኔታ ጋር የተመሳሰለበት ምክንያቱ ምንድነው? ለዚህ መልሱ ምክንያቱ ጉዳይ የታሪክ ብቻ ስላልሆነ ነው የሚል ነው። ታሪኩ የጥንት ብቻ አይደለም። የዚህ ዓይነቱ ክስተት ማብቂያ የለውም። እስከመጨረሻው ድረስ የሚቀጥል ነው። የሁልጊዜም መማርያ ነው። ክስተቶችንም በተመለከተ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል :-

﴿ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَآيَةً ۖ وَمَا كَانَ أَكْثَرُهُم مُّؤْمِنِينَ ﴾

**«በዚህ ውስጥ ታላቅ ተዓምር አለበት፤ አብዛኞቻቸውም አማኞች አልነበሩም።»**

(አሽ- ሹዐራእ : 67)

አዎን ታሪክ ምልክትም፣ ተዓምርም፣ መማርያም ነው። የአላህ መኖር ምልክት። የዚህ ዓለም ምስጢር። አምባገነኖች መቼም እንደማያሸንፉ ታላቅ የማሳያ ተዓምር። አማኞችን የሚያጋጥሙ መሰናክሎችና ችግሮች የምር እንዳልሆኑ መግለጫ። ችግሮቹ እውነት አይደሉም። ቢገፏቸው በቀላሉ የሚወድቁ ናቸው። የተፈጠሩትም ለፈተና ነው፣ እኛን ለመሞከር። እኛን ከወንጀላችን ለማፅዳት። በዚህ መልኩ ታልፎ ነው አብዛኛው ድል የሚገኘው። በአደገኛ ወጥመድ የተያዝን፣ የተሸነፍን፣ ጉልበት ያጣን በመሰለን ጊዜ አስቸጋሪ ነገሮችን ሁሉ ማለፍ እንደምንችል ማሳያ ነው። ለዚህም እይታችንን ማስተካከሉ ወሣኝ ነው። ከመሰናክሎች ባሻገር አላህን መመልከት።

አንዳንዶች ሊጠይቁ ይችላሉ። በርግጥም አምላካችን ከኛ ጋር ከሆነ በቀላሉ የማናሸንፈው ለምንድነው?። አንዳንዶች ይገረማሉ። ያለ አንዳች ትግል እና የመስዋእትነት ክፍያ አላህ ተገቢውን ድል ለሐቀኞች የማይሠጠው ለምንድነው? ይላሉ። .. ለዚህ ጥያቄ መልሱ በአላህ (ሱ.ወ.)ተሠጥቷል።



CS CamScanner

CS CamScanner

አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَمَآ أَرۡسَلۡنَا فِي قَرۡيَةٖ مِّن نَّبِيٍّ إِلَّآ أَخَذۡنَآ أَهۡلَهَا بِٱلۡبَأۡسَآءِ وَٱلضَّرَّآءِ لَعَلَّهُمۡ يَضَّرَّعُونَ ﴾

**«በከተማ አንድንም ነብይ አልላክንም፤ ሰዎችዋን ይዋደቁ ዘንድ በድህነትና በጉዳት የያዝናቸው ብንሆን እንጂ።»** (አል-አዕራፍ : 94)

አላህ (ሱ.ወ.) እንደሚነግረን የፈተና ዓላማው ሰዎች ወደ አላህ ተዋድቀው ወደርሱ እንዲመለሱ ለማድረግ ነው። ይህም ሁኔታ "ተዶሩዕ" ይባላል። ከመተናነስ ያለፈ መዋደቅ፣ አላህ (ሱ.ወ.) ፊት ራስን ማዋረድ፣ ዝቅ ማለት።

ጽንሰ ሀሳቡን ለመረዳት ያህል ለምሳሌ በውቅያኖስ መሃል ብቻህን ጀልባ ላይ እያለህ ከባድ ማዕበል ተነሳና ከበበህ። ግዙፍ ተራራ የሚያህል ወጀብ ሊያሰጥምህ ተቃረበ። በዚህን ጊዜ ያንተ ምርጫ የሚሆነው ወደ አላህ (ሱ.ወ.) መዋደቅ ብቻ ነው። የአላህን እርዳታ መማፀን ነው። በዚህ ጊዜ በምን ዓይነት መልኩ አላህን ልትለምን እንደምትችል አስብ። ያ ትልቅ መዋደቅ ተዶሩዕ ይባላል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዳለውም የዚህ ዓይነቶቹን አስፈሪ ክስተቶች የሚያመጣብን ያንን መዋደቅን ሊሠጠን ነው። አላህ (ሱ.ወ.) ነገሮችን ሊያከብድብን ወይም ደግሞ እኛን ሊሰብረን አይደለም እንዲህ የሚያደርገው። ወደርሱ ይበልጥ ሊያቃርበን ዕድል ሊሰጠን ነው። እንዲያ ካልሆነ መቼም አናስታውሰውም ነበር።

እጅግ መተናነስ፣ ወደ አላህ መቃረብ እና ፍጹም በሆነ መልኩ ወደ አላህ መቃረብ አላህ (ሱ.ወ.) በፈተና ምክንያት ለሕዝበ ሙስሊሙ የሠጠው ፀጋ ነው። አላሁ አክበር!!። አላህ ትልቅ ነው። ግና አላህ የችግር የመከራና የትግልን ሌላ ዓላማ ሲገልጽ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَقَطَّعۡنَٰهُمۡ فِي ٱلۡأَرۡضِ أُمَمٗاۖ مِّنۡهُمُ ٱلصَّٰلِحُونَ وَمِنۡهُمۡ دُونَ ذَٰلِكَۖ وَبَلَوۡنَٰهُم بِٱلۡحَسَنَٰتِ وَٱلسَّيِّـَٔاتِ لَعَلَّهُمۡ يَرۡجِعُونَ ﴾

**«(የእስራኤልን ልጆች) በምድር ላይ የተለያዩ ሕዝቦች አድርገንም ከፋፈልናቸው። ከእነሱ መልካሞች አሉ። ከእነሱም ከዚያ ሌላ አሉ። ይመለሱ ዘንድም በተድላዎችም በመከራዎችም ሞከርናቸው።»**

(አል-አዕራፍ : 168)

በኣሊ ዒምራን ምዕራፍ ደግሞ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፡-

﴿ إِن يَمۡسَسۡكُمۡ قَرۡحٞ فَقَدۡ مَسَّ ٱلۡقَوۡمَ قَرۡحٞ مِّثۡلُهُۥۚ وَتِلۡكَ ٱلۡأَيَّامُ نُدَاوِلُهَا بَيۡنَ ٱلنَّاسِ وَلِيَعۡلَمَ ٱللَّهُ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَيَتَّخِذَ مِنكُمۡ شُهَدَآءَۗ وَٱللَّهُ لَا يُحِبُّ ٱلظَّٰلِمِينَ ١٤٠ وَلِيُمَحِّصَ ٱللَّهُ ٱلَّذِينَ



CamScanner
CamScanner

ءَامَنُوا۟ وَيَمْحَقَ ٱلْكَـٰفِرِينَ ﴿١٤١﴾ أَمْ حَسِبْتُمْ أَن تَدْخُلُوا۟ ٱلْجَنَّةَ وَلَمَّا يَعْلَمِ ٱللَّهُ ٱلَّذِينَ جَـٰهَدُوا۟
مِنكُمْ وَيَعْلَمَ ٱلصَّـٰبِرِينَ ﴾

**«ቁስል ቢያገኛችሁ ሰዎቹንም መሰሉ ቁስል አግኝቷቸዋል። ይኽችንም ቀናት በሰዎች መካከል እናዘዋውራታለን። (እንድትገሰጹና) አላህም እነዚያን ያመኑትን እንዲያውቅ (እንዲለይ) ከእናንተም ሰማዕታትን እንዲይዝ ነው። አላህም በዳዮችን አይወድም። አላህም እነዚያን ያመኑትን (ከኀጢአት) ሊያነጻና ከሓዲዎችንም ሊያጠፋ ነው። በእውነቱ አላህ ከናንተ እነዚያን የታገሉትን ሳያውቅ (ሳይለይ) ታጋሾቹንም ሳያውቅ ገነትን ልትገቡ አሰባችሁን?»** (ኣሊ ዒምራን : 140-142)

እዚህ ላይ አላህ (ሱ.ወ.) የችግር ዓላማው "ተምሒስ" መሆኑን ነግሮናል። ተምሒስ ማለት ወርቅን በእሣት አግሎ በማቅለጥ ንፁሕ ወርቅ አንጥሮ ከማውጣት ጋር የሚመሳሰል ነው። ወርቅ ምንም እንኳ እጅግ ውድ የሆነ ማዕድን ቢሆንም ካላቀለጡትና ከሌሎች ከተቀላቀሉት ብረቶች ካልለዩት ዋጋው ርካሽ ነው የሚሆነው። "ተምሒስ" በማድረግ ማጥራት ይቻላል። አላህ ከምእመናን አንፃር የሚያደርገውም ይህንኑ ነው። ልክ እንደ ወርቅ ሁሉ እኛን ለፈተናና ለችግር በመዳረግ ከተለያዩ ቆሻሻዎች ያፀዳናል።

ብዙውን ጊዜ ጠላታችንና በኛ ላይ ኃይል ያለው ከኛ ውጭ እንደሆነ እናስባለን። ይህ ግን ስህተት ነው። ሁላችንም ጠላታችን በውስጣችን ነው ያለው። ከውጭ ያሉ ጠላቶቻችን በሙሉ የውስጥ በሽታችን ነፀብራቆች ናቸው። ስለሆነም እነዚያን ጠላቶቻችንን ማሸነፍ ከፈለግን መጀመርያ የውስጣችንን ጠላት ማሸነፍ ይኖርብናል። ለዚህም ነው አላህ (ሱ.ወ.) በቁርኣን እንዲህ የሚለን፦

﴿ لَهُۥ مُعَقِّبَـٰتٌ مِّنۢ بَيْنِ يَدَيْهِ وَمِنْ خَلْفِهِۦ يَحْفَظُونَهُۥ مِنْ أَمْرِ ٱللَّهِ ۗ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يُغَيِّرُ مَا بِقَوْمٍ حَتَّىٰ
يُغَيِّرُوا۟ مَا بِأَنفُسِهِمْ ۗ وَإِذَآ أَرَادَ ٱللَّهُ بِقَوْمٍ سُوٓءًا فَلَا مَرَدَّ لَهُۥ ۚ وَمَا لَهُم مِّن دُونِهِۦ مِن وَالٍ ﴾

**«ለእርሱ (ለሰው) ከስተፊቱም ከኋላውም በአላህ ትዕዛዝ (ከክፉ) የሚጠብቁት ተተካኪዎች (መላእክት) አሉት። አላህ በሕዝቦች ዘንድ ያለውን ጸጋ በነፍሶቻቸው ያለውን (ኹኔታ) እስከሚለውጡ ድረስ አይለውጥም። አላህም በሰዎች ላይ ክፉን በሻ ጊዜ ለእርሱ መመለስ የለውም። ለእነርሱም ከእርሱ ሌላ ምንም ተከላካይ የላቸውም።»** (አር-ረዕድ :11)

ስስትን ማሸነፍ አለብን፣ ራስ ወዳድነትን፣ በአላህ ማጋራትን፣ የተጋነነ ፍራቻን፣ ፍጹም በሆነ መልኩ ከአላህ ውጭ ማፍቀር፣ ተስፋ ማድረግንና በሌሎች ላይ ጥገኛ መሆንን ማስወገድ መቻል አለብን። የበሽታዎች ሁሉ ምንጭ የሆነውን አለቅጥ ዱንያን መውደድን



CamScanner
CamScanner

ማሸነፍ አለብን። እንዲሁም ሌሎች የጨቆኑን እና የተጫኑንን ነገሮች ሁሉ ማሸነፍ አለብን። ከውጭ ያለውንና በሕይወታችን ጣልቃ ገብቷል ብለን የምናስበውን ፊርዐውንን ለማሸነፍ ከማሰባችን በፊት በውስጣችን ያለውን አምባገነን ማሸነፍ አለብን። ከራሣችን ጋር በሚደረግ ጦርነት መጀመርያ ራሣችንን ነፃ ማውጣት መቻል አለብን። በትክክል የተጨቆነው ሌላ ሳይሆን እኛው ራሣችን ነን። በዋናነት የጨቆነንም ራሣችን ራሱን ነው። ኢብኑ ተይሚያ ለዚህ የሚሉት አላቸው።

"በእውነት የታሰረ ማለት ቀልቡ ከአላህ የታሰረ ነው። ምርኮኛ ማለትም የራሱ ስሜት ባርያው ያደረገችው ነው።" (ኢብኑ አልቀዪም - አል-ዋቢል ውስጥ እንዳሠፈሩት።)

በውስጥህ ነፃ ስትሆን፤ መጥቶ ነፃነትህን ይቀማ ዘንድ ለማንም አትፈቅድም። በውስጥ ነፃነት ሲሰማህ ከአምባገነኖችና አብሪተኞች በሻገር የነሱ ጌታ የሆነውን አምላክ የማየት ኃይል ይኖርሃል። በውስጥህ ነፃ ስትሆን በቀላሉ ባርያ አትሆንም። ምክንያቱም ባርያ የምትሆነው ከተሳሰርከው አምላክህ ጋር ብቻ ነውና። ይጎዳኛል፣ አሊያም ይከለክለኛል የምትለው ከአላህ ውጭ አታስብ። ማንም ምንም ነገር ሊወስድብህ እንደማይችል ይገባሃል። አንድን ነገር ሊወስድብህ የሚችለው ብቸኛው አካል አላህ (ሱ.ወ.) ብቻ መሆኑን ታውቃለህና። አምባገነኖችን የሚታገሉ ሁሉ አስተሳሰባቸው እንዲሁ ነው። አላህ እንጂ ባለሥልጣናት እንደማይጎዷቸው ያውቃሉ። እነሱ አላህን እንጂ አምባገነኖችን አይፈሩም።

ለእውነተኛ ድል ቀመሩ በአላህ (ሱ.ወ.) ተነግሮናል፡- ሁለት ነገሮች ማለትም ትዕግስት (ሶብር) እና ተቅዋ (የአላህ ፍራቻ) ናቸው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱصۡبِرُواْ وَصَابِرُواْ وَرَابِطُواْ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ لَعَلَّكُمۡ تُفۡلِحُونَ ﴾

**«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ታገሱ ተበራቱም። (በጦር ኬላ ላይ) ተሰለፉም። ትድኑም ዘንድ አላህን ፍሩ።»** (ኣሊ ዒምራን : 200)

ስለሆነም ውስጣችንን ሳናፀዳ የምናገኘው ድል የለም። ለዚህም ውስጣችንን መፈተሽና ማፅዳት ግድ ይለናል። ይህ ሲሆን ራሣችንና ሕይወታችንን መቀየር የምንችለው። የመፈጠራችንን ዓላማ የምናሳካው በዚህ መልኩ ነው።



CamScanner
CamScanner